ወንጀለኛው ጉዞ
ከሃማ ቱማ እንደፃፈው
በልጅግ አሊ እንደተረጎመው

- „ጠፍረህ እሰረው ይህንን ወንጀለኛ " „ደግሞም እንዳይጮህ አስቁመው" ብሎ ጮኸ ዳኛ ሐጎስ በቀል በተሞላበት ሁኔታ።

- ፖሊሱ ኤኬ 47 ጠበንጃውን ጀርባው ላይ እያስተካከለ የማሽሟጠጥ ፈገግታ የሚያሳየውን የደከመ እስረኛ ፀጥ ሊያስደርገው ቀረበው።በእራፊ ጨርቅ አፉን በመጎስጎስ ዝምም አሰኘው።ዳኛ ሐጎስ ደም የለበሰ አይኑን እያጉረጠረጠ አቃቤ ሕጉን ቀጥል ብሎ አዘዘው።ዳኛ ሐጎስ ቀጭን ሲሆን ሹል አፍንጫውን ችግር የገረፈው ፊቱን ለተመለከተ ምንም አስተያየትና ምህረት ከሱ አይጠብቅም።

- „እስረኛው ሰዓት በማቃጠል የሰለጠነ ነው" ብሎ ጀመረ ቀጭን የሚያሳቅቅ ድምፅና የጮመ ፊት ያለው አቃቤ ህግ ጨርቅ ወደ ጎረሰውና በፊጥኝ ወደ ታሰረው እስረኛውን በመጠየፍ በመመልከት። „አምስት ወር ሞላን እያንዳንዶን ክስ በመካድና ንፁህ ነኝ ብሎ ፍርድ ቤቱን ለማሳምን ሲጥር"።አቃቤ ህጉ የተድቦለቦለ ጣቱን በእስረኛው ላይ በመቀሰር „ይህ ወንጀለኛ የተገኘው በቆራጥ ታጋዮች ከክልሉ ውጭ ካለ ፈቃድ ሲዘዋወር ነው።ይህም በህግ የተደነገገውን ማንኛውም ሰው ከክልሉ ውጭ እንዳይዘዋወር የሚለውን ህግ በመጣስ ነው። ወንጀሉ በሚነገረው ጊዜ ደግሞ እንደገና በሱ ብሶ፦

> „ደዬሳ ወይ ዝዋይ ውስጥ ነን እንዴ ያለነው? በሃገራችን እንደፈለግን መዘዋወር አንችልም እንዴ"?„ይህ መንግስት ማጎሪያ ካምፕ ውስጥ እያኖረን አንድም የፖለቲካ እስረኛ የለንም ይላል ደግሞ"

በማለት መንግስትን የሚቃወም እንኪያ ስላምትያና ከፖሊሶቹ ገጥሞ ነበር።መንግሰት ላይ ጥላቻ የተሞላበት ንግግርም አደርጎም ነበር።ፖሊስ እንዳስረዳውም ከሆነ ፊቱ ትምክህተኝነት የተሞላና እልክም የተቀላቀለበት ነበር ። የጥላቻ አስተሳሰብ እንዳለውም ታይቶበት ነበር።ይህ ወንጀለኛ በሃገሪትዋ ውስጥ የሚገኙትን ብሄረሰቦችን ነፃ ያወጣውንና በክልላቸው ብቻ የመዘዋወር መብት የሰጣቸውን ህግ ተቃውሟአል"።

- „በነገራችን ላይ ክሱ ምንድነው"? ብሎ ትግስት ባጣ ሁኔታ ዳኛ ሃጎስ ጠየቀ ።

- „ወንጀለኛ ጉዞ" አለ ከወረቀት እያነበበ አቃቤ ህጉ። „ወንጀለኛ ንቅናቄ፣ ፀረ አብዮት ቅስቀሳ ፣ ላለመታሰር መገርገር ፣ ፀረ ሰላም ሃሳብ ፣ የመንግስትን አብዮታዊ የብሄረሰቦችን ፖለቲካ መቃወም፣ ክቡርነትዎ እንደተገነዘቡት የፍርድ ቤቱን ሰዓት ማቃጠል፣ በተደጋጋሚ የንቀትና አሽሞጣጭ ፈገግታ ማሳየት። ባጠቃላይ መንግስትን መቃወም።

- „ምን አይነት ፍርድ ነው የምትጠብቀው"? ብሎ ጠየቀ ዳኛ ሀጎስ።ዳኛ ሀጎስ እንደሁልጊዜውም የረጅም አመታት እስር ፍርድ መስጠት ቢወድም

የፍርድ ቤት ስነ ስርአት ግን ለርሱ አስልቺ ነው ። በዳኛ ሃጎስ አስተሳሰብ ሁሉም ሰው ፍርዱ ቀድሞ የተሰጠ መሆኑን ስለሚያውቅ ማንንም ማታለል አይቻልም ብሎ ያምናል። የበላይ ባለስልጣናት ግን የውጭ እርዳታ ለማግኘት የፍርድ ቤቱ ስነ ስርዓት አስፈላጊ መሆኑን ስለገለፁለት ዳኛ ሃጎስ ሳይወድ በግድ እየሰለቸውም ቢሆን የፍርድ ቤቱን ስነስርአት ያካሂዳል።ዳኛ ሃጎስ ችግርን አይቶ ያደገ ስለሆነ በስተርጅና ያገኘው እንጀራ ላይ ለመትፋት አይሞክርም ።በተቻለው መጠን ጥሩ ትያትር ለማሳየት ቢሞክርም እፊቱ ላይ ግን ጭንቀቱ ይነበብበታል ።

- „መንግስት የመጨረሻውን ቅጣት ነው የሚጠይቀው“ አለ አቃቤ ህጉ „ „76 አመት ፅኑ እስራት ከከባድ ስራ ጋር ነው„።

- ዳኛ ሃጎስ ፈልቀቅ አለ።

- „መቼም አንዳንድ አሽሞጣጮች አይጠፉም ማንም የዚህ አገር ዜጋ 76 አመት አይኖርም የሚሉ ። ጉዳዩ ግን እስከመጨረሻ ድረስ ዝዋይ ታጉሮ እዛው ህይወቱ እንድታልፍ ነው።ምህረት ለዚህ ወንጀለኛ አይገባውም“ አለ አቃቤ ህጉ ።

- ትንሽ የሆነውንና ተጠራጣሪ ፊት ያለውን ለተካሳሽ የቆመውን ጠበቃ አንድ ጊዜ ገልመጥ አድርጎ ምስክሩን አስገባው ብሎ አዘዘ“ ። ዳኛ ሃጎስ።

- የመጀመሪያው ምስክር ገብቶ ምሎ የምስክር ቦታውን ያዘ።

- „ ፓሊስ ነህ አይደለህም“? ብሎ ምስክሩን አቃቤ ህጉ ጠየቀ።

- የፓሊስ ልብስ የለበሰው ምስክር „ነኝ“ ብሎ መለሰ።

- „ ለመጀመሪያ ግዜ እስረኛውን ያገኘኸውን የት ነው“።

- „ እስረኛውን አላውቀውም አለ „ ፓሊሱ

- አቃቤ ህጉ ፈገግ ብሎ "ይገባኛል አንተ እሱን እንደጓደኛህ ታውቀዋለህ ማለቴ አደለም። እሱ እስረኛ ነው አንተ ደግሞ ፓሊስ ነህ ። እንዴት ነው እሱ መንገዱን አቁርጦ በአንተ በኩል የመጣው“።

- „እሱ እኔ ባለሁበት አልመጣም። እኛ ነን በሱ በኩል ሄደን ያሰርነው።ፓሊስ ገብሩ ከኔ ጋር ነበር“።

- „ለምን አሰራችሁት ታዲያ“?

- „ከክልሉ ውጭ ሲዘዋወር ስለተገኘ“።

- „እንዴት አወቃችሁ በሌላ ክልል መገኘቱን“?

- „ተነገረን“።

- „ማነው የነገራችሁ“?

- „ሲከታተሉት የነበሩት የደህንነት ሰራተኞች ናቸው“።

- „ለምንድን ነበር የሚከታተሉት“ ?

- „እሱን አልነገሩንም ግን እንደሚመስለኝ ወንጀለኛ ስለሆነ ይመስለኛል“።

- „ይህ ወንጀለኛ ነው የታወቁት የክልል ተቆጣጣሪ የደህንነት ሰራተኞች ይከታተሉት የነበረው። በማንአለኝበት ህግ ጥሶ በማይገባወው ክልል ሲጓዝ ነው የተገኘው“።አለ አቃቤ ህጉ ጥያቄ ይሁን ማስረዳት ግራ በሚያጋባ ሁኔታ።

- ፓሊሱ ምን መመለስ እንዳለበት ግራ ገብቶት እንዳለ አቃቤህጉ „አሁን ፓሊስ ገብሩ የት ነው?“ ብሎ ጠየቀ።

- „ ታሞ ፓሊስ ሆስፒታል ነው ያለው።“

- „ወደ ሆስፒታል የሄደው በዚህ እስረኛ ቅስም ሰባሪ ቃላት የተነሳ ነው“ ?

- „በአውቶቢስ ነው የሄደው እነርሱ እንደሚሉት ከሆነ የምግብ መመረዝ ነው።

- „አሃ መርዝ „ ሊያያዝ የሚችል ወንጀል ነው በሚል አመለካከትና ጥርጣሬውን ለማሰስገንዘብ ወንጀለኛውን እያየ።“እሱ ላይ በኋላ እንመለሳለን።ለምንድነው ታዲያ እስረኛውን ያሰራችሁት“?

- „እንደተናገርኩት እንድናስረው ተነግሮን ነው“።አለ ፖሊሱ።

- „ ምን ምክንያት ነው  እንድታስሩት ያስገደዳችሁ?“ብሎ ጠየቀ አቃቤ ህጉ።

- „ያስገደዳችሁ?“ ግራ በመጋባት ፖሊሱ ጥያቄውን በጥያቄ መለሰ።

- ማለቴ ከክልል ውጭ ሲዘዋወር ። አልተዘዋወረም?

- „ አዎ ተንቀሳቅሶአል“

- „ወንጀል ነው አደለም እንዴ“ ?

- „ነው እንጂ ጌታዬ“።

- „ባለፈው መንግስት ይህ ወንጀል ነው „?

- „አልነበረም“።

- "ሰዎች በመላው አገሪቱ ካለምንም ጠያቂ እንዲዘዋወሩ ይደረግ ነበር" ብሎ እራሱን እየነቀነቀ ቀጠለ አቃቤ ህጉ። "በአሁኑ ግዜ ያገኘነውን ልናመሰግን ሲገባን ይህንን የመሰለ ህግ የሚጥሱ እንደዚህ አይነት ተውሳኮች አይጠፉም። ለመሆኑ ምንድነው  ያላችሁ በምትይዙት ግዜ ?"

- „እኔ ኢትዮጵዊ ነኝ በሃገሪቱ ውስጥ እንደፈለግሁ መዞር እችላለሁ ነው ያለን“።

- „እስፓርተኛ ነው እንዴ? የሚሮጠው ለእንጀራው ነው“?

- „አስተማሪ ነው አሉ“

- „አሃ አስተማሪ“ ብዙውን አስተማሪ እንደመጠርጠር አይነት ፊት እያሳየ። ስራ ፈት አገሪቷን በሞላ ሊዞር የሚፈልግ ወንጀለኛ ነው። ለምን ችግርን በሩጫ አያመልጣትም። ወንድ ከሆነ ለምን እንደ ኃይሌና እንደ ቀኔንሳ ሚሊዮን ለማግኘት አንሮጥም?“።

- „ለመሆኑ ከክልሉ ውጭ እንዴት ነበር የሚንሸራሸረው“?።

- "ምን ማለትዎ ነው አልገባኝም አለ ፖሊሱ

- "ማለቴ እጁን እኪሱ ከቶ እየዘነጠ ነው ፣በኩራት እየተዘባነነ፣እንደቀብራራ አንገቱን ቀስሮ፣ እንደትምክህተኛ ተኮፍሶ፣ አይኑን አፍጥጦ እንደተናደደ ሰው፣ እንደ እርጉዝ ዝሆን ቀስ እያለ፣ ቀን እንደሰጠው ዘናጭ በጫማው ጫፍ መሬትን መርገጥ እንደተጠየፈ ፣ እንደ ምስኪን ስለት ቤተክርስትያን ለማድረስ እንደቸኮለ፣ እንደተገራ ፈረስ በሶምሶማ፣ እንደሚከታተሉት ወንጀለኛ እየተጋላመጠ፣ እንደጠገበ አህያ እያናፋ ፣ እንደ ደላው ሰው እየተንጎራደደ፣ እንደ አዲስ እንደደረሰች ልጃገረድ እየትሸኮረመመ ፣ ወይንስ ጊዜ እንደሰጠው እየተጎማለለ፣ ለመሆኑ የዚህ ጥጋበኛ ጉዞ እንዴት ነበር?። "

- ፓሊሱ ግራ ገብቶት ላብ ያጠመቀውን የተነፋ ጎማ የሚመስለውን አቃቤ ህግ እያየ "እኛ ብዙ አልተከተተልነውም እንደሚመስለኝ ግን አካሄዱ ተልዕኮ ያለው ይመስላል"።

- „ልክ ነህ ይህ ትምክተኛ ህግ ለመጣስ ነው ይከንፍ የነበረው „ ብሎ አቃቤ ህጉ ሲጮህ ዳኛ ሃጎስ እስረኛ ላይ ማንም ሲጮህ ደስ ይለው ነበርና እወንበሩ ላይ ይዝናና ጀመር። "አሁን እንደገና ተመልሰን አረማመዱ እንናገር ። ምን አይነት ጉዞ ነበር የሚጓዘው ልትነግረኝ ትችላለህ ። የትምክተኛ ነው በንቀት የተሞላ፣ እንደ ሰለጠነ ወታደር እጁን እያወናጨፈ፣ ታኮ ጫማ እንደደረገች ሴት ሰበር ስካ እያለ ፣ ሚኒስከርት እንደለበሰች እግርና እግሩን ቀልፎ ፣ ወይስ የቁብ ገንዘብ እንደሞላለት ትራፊክ በፈገግታ ፣ በል ንገረኝ የሚየደርገውን ጉዞ „? አለ አቃቤህጉ ።

- ዳኛ ሃጎስ ቀበል አድርጎ እየተዝናና „ ምንም ፓሊስ ብትሆን አንዳንዴ ማሰብ አለብህ።አስብና ንገረን ምን አይነት ጉዞ እንደተጓዝ ?"

- ፓሊሱ ግራ ገብቶት አንዴ አቃቤ ህጉን አንዴ እስረኛውን ተመልክቶ „ አሁን ሳስታውሰው አደገኛውን ወንጀለኛ ጉዞ ነበር የሚያደርገው። የጎሳ ፖለቲካን የሚቃወም የክልል ፖለቲካን የሚያጣጥል ጉዞ ነበር የሚያደርገው"። አለ ዳኛውን ያስደሰተ ስለመሰለውና የእስረኛው ጦስ እሱ ላይ እንዳይመጣ እየፈራ።

- አቃቤ ህጉ ፈገግ ብሎ „ይህ ወንጀለኛ የተከለከለውን ክልል የጣሰ ወንጀለኛ ጉዞ ማድረጉ ግልፅ ነው። ካልተቀጣ በስንት ትግል ያገኘነውን የክልል ፓለቲካ በትንሽ ግዜ ውስጥ እሱና መሰሎቹ ድምጥማጡን ሊያጠፉት ይችላሉ።ወንጀለኛው ጉዞ የሚያጠቃልለው ፍጥነት ያለበት ተጠርጣሪ ጉዞ ነው።ከአንድ ክልል ወደ ሌላኛው አለፈቃድ መጓዝ ነው። የሚያስፈራ፣ የሚያስደነግጥ፣ ልብን የሚያሸብር ነው። ከዚህ በፊት ይህን ወንጀለኛ ጉዞ ዛሬ በየእስርቤቱ በታጎሩት ፀረ ሰላሞች አይተነዋል። ለመሆኑ ኮንሰንትሬሽን ካንፕ ዝዋይ ወዘተ ብሎ አልነበረም እንዴ" ? ብሎ አቃቤ ህጉ ፖሊሱን ጠየቀው።

- „አዎ ጠይቆ ነበር-- ኮንሰንትሬሽን ካንፕ ውስጥ ነው ወይ የምንኖረው ብሎ ነበር"።

- „እናንተ ምን ብላችሁ መለሳችሁለት" ?

- „እንዲህ አፉን ከከፈተ እሱ የሚላቸው ኮንሰንትሬሽን ካንፕ ውስጥ ወስደን እንደምንከተው ነገርነው"።

- አቃቤ ህጉ ጉሮሮውን በሳል ከአፀዳ በኋላ „ ማለትም ይህንን የመሰለ ወንጀለኞች ናቸው ጥሩ አስተዳዳሪዎችን እንደዚህ አይነት እስር ቤቶችን እንዲከፍቱ የሚገፋፉት። "

- "እኛም ነግረነዋል እንዲህ ከቀጠልክ ደዴሳ ፣ ሸዋ ሮቢት ፣ ወይም ዝዋይ እንደምንልከው ነግረነዋል" በመደነቅ ምስክሩ ተናገረ።

- "ይመዝገብልኝ ጌታዬ" አለ ወደ ዳኛው በመደንገጥ እያፈጠጠ አቃቤ ህጉ። „ይህ ምስክሩ የጠቀሳቸው ቦታዎች በጥሩ ሁኔታ በተመጣጠነ ምግብ ማለትም በቀን ትንሽ ዳቦና አንድ ብርጭቆ ውሃ እየተሰጣቸው ፀባያቸውን እንዲያርሙ ከዛም ወደ ህብረተሰቡ እንደየ ክልላቸው እንዲቀላቀሉ ሲባል የተቋቋመ ነው“።

- ለመስቀለኛ ጥያቄ የተከሳሽ ጠበቃ ተነሳ ።

- „ከክልላቸው የሚወጥቱን ሁሉ ታስራለችሁ ማለት ነው“?

- „ምን ማለትዎ ነው ይህንማ ካደረግን እስር ቤቱ አይበቃንም ።ይህማ የሚቻል አደለም“።

- „ታዲያ እየመረጣችው ነው የምታስሩት ማለት ነው“?

- „አዎ“

- „ታዲያ የሚታሰረውን ማነው የሚወስነው“?

- „ከአለቆቻችን ነው ትእዛዙን የምናገኘው“።

- „እስረኛውን እንድታስሩት ትህዛዝ አግኝታችኋል ማለት ነው“?

- „አዎ አግኝተናል“።

- „ትእዛዙን ያገኛችሁት የተባለውን ወንጀለኛ ጉዞ ሲያደርግነው ወይስ ገና ሳያደርግ“?

- „የደህንነቱ ሰውዬ እንድናስረው ሲነግረን እሱ የተባለውን ጉዞ እየተጓዘ ነበረ“።

- "ለእናንተ ልዩነት አልነበረውም እንደውፍሮ ቤት በግ ቢንቀዋለል ወይም በትምክህት ቢጓዝ። ክልሉን ቢጥስ ባይጥስ እስሩ ስለተባለችሁ ማሰር ነበረባችሁ አደለም እንዴ ?"

- „የወፍሮ ቤት በግ ይንቀዋለላል እንዴ „? አለ የሽሙጥ እየሳቀ።

- የተከሳሽ ጠበቃ „ይመዝገብልኝ ተከሳሹ ከክልሉ ቢወጣም ባይወጣም ይታሰር እንደነበር“።

- „ተቃውሞ“ አለ ተነስቶ አቃቤ ህጉ „የተከሳሽ ጠበቃ ይህንን ሊል አይችልም። ምስክሩ በኔ የተጠራ ስለሆነ ይህ መብት የኔ ነው“።

- የሚቀጥለው የአቃቤ ህግ ምስክር በመካከለኛ እድሜ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን አገጩ ስር ያለው ስጋ የተንጠለጠለ ስለሆነ ትንሽ የሚያስቅ ፍጡር ያደርገዋል ።

- „ሙያህን ለፍርድ ቤቱ ልታስረዳ ትችላለህ አለው“?አለው አቃቤ ህጉ አዲሱን ምስክር እየተመለከተ።

- „እኔ መርማሪ ፖሊስ ነኝ“።

- „ስንት ግዜህ ነው በዚህ ስራ ላይ“?

- „ሃያ አምስት አመቴ ነው ጌታዬ“።

- „ካለጥርጥር በሙያው ተክነሃል“ ። አለ አቃቤ ህጉ አይኑን ተለቅ አድርጎ ማድነቁን ለመግለጽ።“ምንም አይነት ወንጀል አንተን ሊያመልጥህ አይችልም አይደለም“ ?

- „ውሸት ከመነገሩ በፊታ አውቃለሁ“ ። አለ መርመሪው ጉራ በተመላበት ሁኔታ ።

- „እስረኞችን የምታውጣጣበትን ዘዴ አልጠይቅህም። ሌሎች እስረኞች እንዳያውቁት። ግን ባጠቃላይ እስረኞቹን ነው የምትመረምረው“?

- „አዎ ልበለዎት ጌታዬ“ ።

- „ይህን ትምክተኛ እስረኛ ምን እንድትመረምር ነው ትዕዛዝ የተሰጠህ“?

- „ፀረ ሰላምና ፣ ፀረ አብዮት እንደሆነ ነው የተነገረኝ ። በዛ ለይ ደግሞ አስቸጋሪና ጥፋቱን የማያምን መሆኑን ነው“።

- „ከዚህ በፊት እንደዚህ አይነት ወንጀለኞች እናንተ ጋር ሲቀርቡ ወዲያውኑ ጥፋታቸውን አምነው ተቀብለዋል“ ?

- „ጌታዬ ለመሆኑ ዝንጀሮ እሽታለሁ ብሎ ያምናል? አንዳንድ ወዲያው የሚያምኑ ቢኖሩም ብዙዎቹ ግን ወፌ ኢላላ ክፍል ካላገባነቸው ፍንክች አይሉም“ ።

- ይህንን ግዜ ዳኛ ሃኀስ በመዝናናት በወንበሩ ከተመቻቸ በኃላ መስማማቱን ጭንቅላቱን በመነቅነቅ ለምስክሩ አሳየው፡፡

- አቃቤ ህጉ „መለመን የለመደ በህልሙም ፍርፋሪ ይለምናል እንዲሉ ልምድ ሆኖባቸው ሁሉም አያምኑም ። እናንተም ይህን አትጠብቁም አደለም እንዴ“? ብሎ ምስክሩን ጠየቀው።

- „እኛም እኮ እንጀራችንን እንፈልጋታለን። ሁሉም ወዲያውኑ ካመኑ መርማሪና ወፌ ክፍል ለምን ያስፈልጋል ብለው ጌታዬ“ ።

- „እውነትንህ ነው አለ አቃቤ ህጉ። ግን አሁን ምርመራው ካለፈው መንግስት ጋር ስታወዳድረው ያሁኑ ሙሉ ሰባዊነት የተሞላበት ነው ብልህ ታምናለህ“?።

- „ያኔም ቢሆን እኔ መራማሪ ነኝ ። ግን አሁን የመንግሰት ካድሬዎች ጫካ በነበሩበት ግዜ ይጠቀሙበት የነበረው የወፌ አይነት ለሶሰት ሳምንት ካስተማሩን በኃላ ይህ ሰብአዊነት የተሞላበት ነው ብለው ነግረውናል ። ለምሳሌ አሁን የመርማሪው ቁጥር ስለጨመረ ማለትም ድሮ እዚህ የነበርነውና ከመንግሰት የተጨመሩልን አንድ ላይ በመሆን ማውጣጣቱን ስለምናደርግ ጠዋትና ሌሊት መስቀልና መግረፍ አቁመናል።በዚህም ላይ ደግሞ የሚገለበጡት እንደበፊቶቹ ጥንካሬ የላቸውም። በተለይ ደግሞ የአሁኑ መንግሰት በድሮው መንግስት ከምስራቅ ጀርመን የተገዛልንን የኤሌትሪክ መሳሪያዎች አደገኛ በማለት በራሱ ክልል ውስጥ ያሰራቸው እስረኞች ላይ ለመጠቀም ወስዶታል። አሁን የምንጠቀመው በጉልበት ብቻ ነው።በጣም ልዩነት እንዳለ ልነግራችሁ እወዳለሁ“ ።

- „እስረኛው በፀረ መንግስት እንቅስቃሴ ውስጥ እንዳለበት አምኖአል“? ብሎ ጠየቀ አቃቤ ህጉ ።

- „አላመነም“ አለ ምስክሩ ። „ቢያምን ኑሮ ወደ ከርቼሌና ወደ ፍርድ ቤት አናቀርበውም ነበር“ ።

- „በምርመራው ወቅት የእስረኛው ባህሪ እንዴት ነበር“ ?

- „የሌባ ልብ አውልቅ መልሶ ልብ ያድርቅ አይነት ነው። አያምንም ችኮ ነው። ለፍላፊ ነው ስለ ህገ መንግስታዊ መብቱ ሲጮህ ነበር። እኔ ግን ህገ መንግሰት የሚለውን እንዳላነበብኩና ካድሬዎቹም እንዳላስተማሩን ነገርኩት። ግዜውንም ለኔ ለማስረዳት እንዳያጠፋ ነግሬው ነበር። እሱም አስተማሪ መሆኑንና መምህራን ማህበር ውስጥ እንዳለበት ነገረኝ። እዚህ ላይ ነው ትልቅ ወንጀል እንዳለ የሸተተኝ። ይህም ወንጀል መሆኑን ነገርኩት። እሱ ደግሞ አውቃለሁ ባይ አይነት ስለሆነ ይነተርከኝ ገባ። በኔ ልምድ ማንኛውም ማህበር እድርና እቁብም ሳይቀር ስውር የሆነ ዓላማ እንዳለው ነገርኩት። በመጨረሻም ይህ ወንጀለኛ ብዙ ሊያወጣ እንደሚችል ተገነዘብኩ“ ።

- „እንዴት እንደሚያወጣ ተገነዘብክ“ ብሎ አቃቤ ህጉ ጠየቀ?

- „በአሁኑ ግዜ የትኛው ኢትዮጳያዊ ነው መንግሰት የሚጠላው ማህበር ውስጥ አለሁበት የሚል ። ጨርቁን ጥሎ የሚንገላወድ እብድ እንኳን ይህን ያውቃል። እብዱ ቢጠየቅ ይህንን አያምንም ። ወዲያው የምርመራውን አይነት መቀየር እንደለብኝ ገባኝ። ወፌ ቢገባና ቢገለበጥ እንደሚያወጣ ገባኝ“።

- „ግን እስከመጨረሻው እኮ አላወጣም“?

- „ፍርድቤቱ እንዲረዳልን የምፈልገው በአሁኑ ግዜ የምንጠቀምባቸው መሳሪያዎች እንደሌሉንና በተራ የወፌ ኢላላ ዘዴ ነው የምንጠቀመው። ይህ ዘዴ ደግሞ ሁሉንም ሚስጥር ያስወጣል ብዬ አላምንም። ወስፌ፣ መቀስና፣ ጉጠት ብቻ በቂ አይደለም።ድሮ እንጠቀምበት የነበረው የፌያሽኮ ጠርሙስ እንኳን እንደልባችን አናገኘውም“።

- ዳኘ ሐጎስ በመቀጠል፡፤ „ምንም እንኳን የመርመሪያ መሳሪያዎቹ በጣም ወደሚያስፈልግበት ቦታ ቢወሰድባችሁም የምትሰሩትን ስራ መንግስት ከማንኛውም በላይ ይገነዘባል። ይህንንም ለማወቅ ወደ መንገዱ ወጣ ብሎ እጅ እግሩ የተቆረጠውና የሚያነክሰውን ማየት ብቻ ይበቃል ። በዚህ እንደምትመለከቱት እስረኛ ያስፈልገናል። ፍርድ ቤቱ ከሌለ የውጭ እርዳታ ደግሞ ሊቆም ይችላል ። እንደምታውቁት ለናንተም የሚከፈለው ከዚሁ እርዳታ ላይ ነው“ ።

- „ጌታዬ" ብሎ መርማሪው ዳኛውን በማየት ቀጠለ ። "እንደውነቱ ከሆነ በአሁኑ ግዜ ወፌ የሚገቡት የሚያፍሩበትና አንገታቸውን የሚያስደፉቸው አይነት ምርመራ አይደለም የምናደርገው። በኩራት አንገታቸውን ቀና አድርገው ሊሄዱ ይችላሉ“።

- „ወፌ በገቡት መካከል ፉክክር አለ እንዴ“ ?አለ ዳኛ ሐጎስ።

- „እንዴታ ጌታዬ! በደርግ ግዜ የተገረፉት እኛ ነን በኃይል የተገረፍን በማለት ሚስጥር ያላወጡት ጠንካራ ስለሆንን ነው እንዳይሉ የአሁኖቹ ምንም የምንፈልገውን ቢያምኑልንም እኛ ግን አንገታቸውን ለወደፊት እንዳይደፉና እኛን እጀ ሰባራ እንዳያደርጉን ጥረታችንን አናቋርጥም“።

- አቃቤ ህጉ እንደገና ምስክሩን "ስለ እስረኛው ምን ታስባለህ“? ብሎ ጠየቀው።

- „ጌታዬ“ አለ ምስክሩ በፈገግታ ታላቅ እውቀት እንደሚናገር ዳኛውን እየተመለከተ „በግን ካላረዱት ስለ ስጋዋ መናገር አይቻልም። አዳጋችና ሞገደኛ ግለስብ ነው ግን ጥፋተኛ መሆኑን አምንበታለሁ ። ወንጀለኛውን ጉዞ አኳሂዱዋል“ ።

- የተካሳሽ ጠበቃ ተነስቶ „ ተከሳሹ በምንም አይነት ቃላት አላመነም“ አለ።

- ምስክሩ የተከሳሹን ጠበቃ እየተመለከተ„ ቃላት እኮ ውድ ናቸው።ቢሆንም የተወሰነ አምኖአል“ ።

- „ምንድነው ያመነው ነው የምትለው ባንተ አስተሳሰብ“ ?

- „የመምህራን ማህበር አባል መሆኑን“ ።

- „መምህራን ማህበር ህጋዊ አደለም እንዴ“?አለ ጠበቃው።

- „ቅድም እንዳስረዳሁት መንግስት ካልወደደው ህጋዊ መሆን ብቻ አይበቃም“።

የአቃቤ ህግ የሚቀጥለው ምስክር ደግሞ እስራኤልና በአሜሪካ የተማረ ዶክተር ነው ።

- „ዶክተር እስረኛውን መርምረሃዋል“ ? ብሎ ጠየቀ አቃቤ ህጉ ።

- „አዎ መርምሬዋለሁ“ አለ ዶክተሩ ፀአረ ሞት በመሰለ ድምጹ “የደምና የስነ ልቦና ምርመራ አድርጌለታለሁ ። ይህም በጣም የረቀቀ ወይን የሚባል የምርመራ ዘዴ ነው“።

- „እውን በወይን የምርመራ ዘዴ የአንድን ግለሰብ ክልልና ጎሳ ማወቅ ይቻላል“?

- „በጣም እንጂ ጌታዬ! እኛ በጣም አስቸጋሪ ነው የሚባለውን ቅይጥ ዘር አለን የሚሉትን መርምረን እርግጠኛ ዘራቸውን አግኝተናል“።

- „የእስረኛው ጎሳው ከታሰረበት አካባቢ ነው ?

- „የደሙና የስነ ልቦናው ምርመራ ከዛ እንዳልሆነ አረጋግጠልናል“ ።

- „ለፍርድ ቤቱ ማስረጃ እንዲሆነን ስለ ሙያዎ ቢያስረዱን“?

- „የኛ የምርመራ ዘዴ በመጀመሪያ የስነ ልቦና ምርመራ እናደርጋለን። ይኸውም የቃላት ጥያቄና መልስ ነው ። ይህንን በመጠቀም ግለሰቡ ከየትኛው ጎሳ እንደመጣ እናውቃለን ማለት ነው። ለምሳሌ እኛ ኢትዮጵያ ስንል እነርሱ የለለ ነገር መናገር ይጀምራሉ ዴሞክራሲ፣ደይኖሰረስ፣ ሴኩሪቲ፣ በቂ ምግብ እና ሌሎችም። ለምሳሌ ይህንን እስረኛ እንመልከት እንዲህ ሲመለከቱት ሀቀኛ ይመስላል ግን እውነቱ ሌላ ነው። ኢትዮጵያ ስንለው ሀገሬ ብሎ መለሰልን ከዚህ በመነሳት የደረስንበት ግለሰቡ ትምክት የተሞላበት የአርበኝነት ፀባይ አለው ማለት ነው። ይህ ደግሞ ከየትኛው ዘር እንደመጣ በቀላሉ ሊያስረዳን ይችላል“።

- ሳይታሰብ የተከሳሽ ጠበቃ ተነስቶ "ይህ ወይን የተባለው ምርመራ በአብዛኛው የህክምና ባለሙያዎች ዘንድ ተቀባይነት አላገኝም። ይህ ትክክል ነው?" ብሎ ዶክተሩን ጠየቀ“።

- „የዘመኑ ሳይንስና ቴክኒዮሎጂ በሁሉም ተቀባይነት ያገኛል ማለት ችግር ነው። አሁንም ቢሆን ይህንን የምርመራ ዘዴ አንቀበልም የሚሉ ትምክህተኞች ይኖራሉ ። ወይን የምርመራ ዘዴ ባንድነት ስም መደበቅን ያጋልጣል። የሰው ፍጡር የተሰራበት ሴል ውስጥ የሚገኘው ክሮሞዞም እየተባለ የሚነገረው የአንድን ግለሰብ የዘር ኢንፎርሜሽንን ይዞ ስለሚገኝ

እሱን በመጠቀም የግለሰቡን ጎሳና አስተሳሰቡን ማወቅ ይቻላል።አንድ አገር ፣ አንድ ሕዝብ የሚባለው ግዜው ያለፈበት መፈክር ነው“።

- የተከሳሽ ጠበቃ „በዚህች አገር ላይ አንድ ኢትዮጵያዊ የሚባል ፍጡር መኖሩን ታምናለህ“? ብሎ ጠየቀ።

- „ይህ አፈ ታሪክ ነው እንደ ድንጋይ ዳቦ ዘመን“።

- አቃቤ ህጉም ሆነ የተከሳሽ ጠበቃ ጥያቄ ስለሌላቸው ዶክተሩ ተሰናበተ።አቃቤ ህጉ ሌላ ምስክር እንደሌለው ለዳኛ ሃጎስ አስረዳ። ይህ ሁሉ ሲሆን እስረኛው አፉ በጨርቅ ተጎስጉሶ፣እግሮቹና እሎቹ ታስረው ነበር። ዳኛ ሐጎስ ፀጥታ ጠይቀው ሁሉም ዝም ሲል ፍ/ርዱን ማሰማት ጀመረ።

„ተከሳሹ እዚህ የቀረበው በሃገሪቱ ውስጥ በወቅቱ የሚሰራባቸውን የወንጀለኛ ህግጋቶች በመጣስ ነው ። አቃቤ ህጉ ይህ ግለሰብ **ወንጀለኛውን ጉዞ** እንዳደረገና ወንጀሉም አደገኛ የሆነ ታስቦበት የተሰራ መሆኑን በማያጠራጥር ሁኔታ አጋልጦታል“ ።

„ግለሰቡ ሰባአዊ የሆነውን ካለፈው መንግሰት በጣም የተሻሻለውን የወፌ ኢላላ የምርመራ ዘዴ ላይ በሚገኝበት ግዜ ከመርማሪው ጋር መተባበር ሲገባው ያልሆነ እንቶ ፈንቶ እያወራ ብሎም መንግስት በጎሪጥ የሚያየውን የመምህራን ማህበር አባልነቱን በተደጋጋሚ በመጥቀስ የመርማሪውን ወርቅ ሰዓት የህገ መንግሰት መብቴ ነው እያለ ሲያባክን እንደነበር ተመስክሮበታል። ተከሳሹ የክልልን ህግ ጥሶል ፣ ፀረ አብዮት ቅስቀሳ አድርጓል ፣ መንግሰት በጥሩ ሁኔታ የማያየው የመምህራን ማህበር አባል ነው፣ አሳፋሪውን ወንጀለኛ ጉዞ አድርጎ ሳለ ይህንኑ ክዶ የፍርድ ቤቱን ወርቅማ ሰዓት መብት፣ ፍትህ በማለት አቃጥሎአል“።

„ዛሬ አንድ ኢትዮጰያ በምትባል ካለ ክልል ልቅ በሆነች አገር መኖር አክትሟል።ዛሬ የተማሩ ዶክተሮች አሉን በደማችን ጎሳችንን ክልላችንን አለችግር ሊነግሩን የሚችሉን ።ይህንን ድል በትግላችን ያገኘነው ነውና እንጠብቀዋለን። እያንዳንዱ በየክልሉ የሚለው መፈክር ሳይንሳዊ ነው።ተከሳሹ የክልልን ህግ ጥሶ ከክልል ወደ ክልል እንደፌንጣ ሲዘል ነበር። በማያጠራጥር ሁኔታ ወንጀለኛውን ጉዞ አደርጓል። ሌሎች ፀረ ሰላም እንቅስቃሴዎችን አስቦአል። በዚህም ምክንያት ፍርድ ቤቱ ለ76 አመት በፅኑ እስራትና በከባድ ስራ እንዲቀጣ ወስኖበታል ። ዳግም ይህን አይነት ጉዞ ሊያደርግ በማይችልበት እስር ቤት ውስጥ እንዲታሰር ተወስኖአል“ ።